በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

‹‹ዘ...ፀ...አ...ት››

✓ ዘፀአት ማለት መውጣት ማለት ነው።

✓ የዚህ መንፈሳዊ ተውኔት መሰረታዊ አላማ፡-

✓ ለዘመናት በእኛ ሕይወት አልሰበር ያለውን የክፋት ደጅ በአምላካችን ኃይል ሠባብረን እንድንጥል እና አሁን ካለንበት በልማድና በሱስ ከተያዝንበት አላስፈላጊ ሕይወት በቆራጥ ውሳኔ እንድወጣ ለማስቻል ነው።

✓ ይህ መንፈሳዊ ተውኔት ሁለት ትዕይንቶች ሲኖሩት የሚሰራውም በሦስት ሰዎች ነው።

‹‹ዘፀአት ትዕይንት አንድ››

✓ ተውኔቱ ሲጀምር ኢሳያስ ደብሮትና ሁሉም ነገር አስጠልቶት መድረክ ላይ ይታያል

✓ ኢሳያስ፡- የዛሬው ቀን ደግሞ ምን አይነት አስቀያሚ ቀን ነው በእናታችሁ ..... /ይንጣራራል ያዛጋል ይንቆራጠጣል/ ለምን ግን እነ ጆኒ ጋር አልደውልላቸውም /ሞባይሉን አውጥቶ ይደውላል/ ሔለው ጆኒ .... የት ናችሁ .... የተለመደው ቦታ .... ሰዓቱ ገና አይደል እንዴ .... ድብር ብሎኝ ከቤትም አልወጣውም ... እሺ ትንሽ ጠብቁኝ እዛው እመጣለው /ፍቅርተ ትገባለች/

✓ ፍቅርተ፡- ሠላም ለዚህ ቤት ይሁን እንዴት ነሕልኝ ኢሴ

✓ ኢሳያስ፡- እግዚአብሔር ይመስገን አለውልሽ /ሰላም ይባባላሉ/

✓ ፍቅርተ፡- ልትወጣ ነበር እንዴ

✓ ኢሳያስ፡- አይ ... ድብር ብሎኝ ከቤት መውጣት አስጠልቶኝ እያለ ነው የመጣሽው

✓ ፍቅርተ፡- እየዋሸሽኝ እንዳይሆን

✓ ኢሳያስ፡- ‰ረ አልዋሸውሽም ... ግን....

✓ ፍቅርተ፡- ግን ምን ኢሴ

✓ ኢሳያስ፡- ስለደበረኝ ከነጆኒ ጋር ተደዋውዬ ልሔድ ስል ነበር የመጣሽው

- ✓ ፍቅርተ፡- ታዲያ እንደዚያ አትለኝም እንዴ
- ✓ ኢሳያስ፡- ትቆጭኛለሽ ብዬ ፈራው
- ✓ ፍቅርተ፡- ለምን ኢሴ ... ከዚህ በፊት ተቆጥቼክ አውቃለው
- ✓ ኢሳያስ፡- በፍፁም
- ✓ ፍቅርተ፡- እሺ እነሱጋ መሔድ ከፈለክ እኔን ወደ ቤት ትሸኘኝና ትሔዳለህ በጣል ስለበረደኝ ግን ይሔን ጃኬት እስከቤት ድረስ እለብሰዋለው /ወንበር ላይ የተቀመጠውን የኢሳያስን ጃኬት አንስታ ትለብሳለች እለቱንም እጆቿን ወደ ውስጥ ስትከት ሁለት ሲጋራዎችን ከኪሱ ውስጥ ታገኛለች/
- ✓ ኢሳያስ፡- ይደነግጣል
- ✓ ፍቅርተ፡- ምነው ደነገጥ
- ✓ ኢሳያስ፡- /እንገቱን አቀርቅሮ ፀጉሩን እያከከ/ አይ ምንም
- ✓ ፍቅርተ፡- ብዙ ጊዜ አቁሜአለው እያልክ ስለዋሸሽኝ ነው አይደለም ይሔውልህ ኢሲዬ ሱስህን በቀላሉ እንደጀመርከው በቀላሉ ትተወዋለህ ብዬ አላምንም .... ግን ያለንተ ማንም የለንም ለእኔም አስብልኝ እባክህን እንድትጎዱብኝ አልፈልግም ቢያንስ ከበፊቱ መቀነስ ይኖርብሃል
- ✓ ኢሳያስ፡- እንዴት አድርጌ ፍቅር

ፍቅርተ፡- በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ፍቅር እንዲገባህ ከልብህ በመፀለይ

ኢሳያስ፡- ጸሎት! በዚህ ሕይወት ውስጥ እያለው ጸሎት

ፍቅርተ፡- እግዚአብሔር ንፁሐ ባህርይ ነው ንፁህ መሰዋዕትም እንደሚፈልግ አውቃለው ቢሆንም ኃጢአተኞችን ሳይሆን ኃጢአትን ነው የሚጠላው የልቦናህን መሻት ከማንም በላይ የሚያው እሱ ነው የራሰህን ሸክም እራስህ ማራገፍ አትችልም እሱ ግን ከድካማችን ሊያሳርፈን ወደ እኔ ኑ ይለናል የእኛ ድርሻ ወደ እሱ መቅረብ ብቻ ነው፡

- ✓ ኢሳያስ፡- ከዚያስ
- ✓ ፍቅርተ፡- ወደ ተሻለው ሕይወት ሊያመጡን የሚችሉትን ቅዱሳት መፅሐፍት አንብብ .... የሕይወትህም መመሪያ አደርጋቸው ትክክለኛ የሕይወት መስታወት መፅሐፍ ቅዱስ ነው በእምነት አንበው እውነተኛውን ጎዳና ያሳይሃል
- ✓ ኢሳያስ፡- ገና መፅሐፍ ቅዱስን ላንብ ስል እኮ እንቅልፍ እንቅልፍ ይለኛል

- ✓ ፍቅርተ፡- አውቃለው ያአንተ ብቻ ችግር ሳይሆን የብዙ ሰዎች ችግር ነው ቁጭ ብለህ ስታነብ እንቅልፍህ ከመጣ ቆመህም ቢሆን አንብብ ተስፋ አትቁረጥ የአንተን ፅናት የተመለከተ አምላክህ አንድ ቀን ያበረታሃል አንተ ግን በውሳኔ ተመላ
- ✓ ኢሳያስ፡- ይሔን አንኮ አሁን ባልሽኝ ሁኔታ ባይሆንም ብዙ ጊዜ አስቤው ሞክሬዋለው
- ✓ ፍቅርተ፡- አውቃለው ያኔ በአንተ ሃሳብና ፍላጎት የተደረገ ሙከራ እንጂ ከጌታ መልካም ፍቃድ የተመሰረተ በውሳኔ የተደገፈ አልነበረም
- ✓ ኢሳያስ፡- እንዴት
- ✓ ፍቅርተ፡- ይሔውልህ ኢሴ ምኞት ፍላጎት ነው ውሳኔ ደግሞ ቆራጥነት። በውሳኔ የተመላ ሕይወት ሊኖርህ ይገባል ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በአንተ ሕይወት ውስጥ ሊሰራ ያሰበውን ስራዎች በሚያስገርም ሁኔታ ሲያከናውን ታየዋለህ ያ እንዲሆን ግን ለመፍረስም ለመታነፅም ለመድከምም ለመብርታትም ያንተ ቆራጥ ውሳኔ ትልቅ ሚና አለው
- ✓ ኢሳያስ፡- ይሄ ይሆናል ብለሽ ታስቢያለሽ
- ✓ ፍቅርተ፡- በሚገባ
- ✓ ኢሳያስ፡- እኔ ግን አይመስለኝም
- ✓ ፍቅርተ፡- ባይመስልህም ቢመስልህም እኔ ግን የእኔ ጌታ የድንግል ልጅ አማኑኤል አንድ ቀን ከሱስ መንደር እንደሚያወጣህ አዲስ አድርጎ እንደገና እንደሚሰራህ አምናለው አንተ ግን ለመታመን ሞክር ታላቁን የሕይወት መፅሐፍ መፅሐፍ ቅዱስን የልብ ጓደኛህ አድርገው ከአንተ የሚየበቀው ይሔ ነው
- ✓ ኢሳያስ፡- ቀሪውስ
- ✓ ፍቅርተ፡- ቀሪው ከእኛ አቅም በላይ ስለሆነ የእግዚአብሔር ሰራ ነው
- ✓ ኢሳያስ፡- /ሞባይሉ ይጮኻል/ ሔለው ጆኒ .... አዎን እስከ አሁን እዛው ናችሁ .... ልወጣ ስል እኮ ፍቅርተ ስለመጣች እኮ ነው የቆየውት .... መቼ አሁን እ...
- ✓ ፍቅርተ፡- መጣው በላቸው /ትለዋለች/
- ✓ ኢሳያስ፡- እሺ መጣው እዛው ጠብቁኝ ....
- ✓ ፍቅርተ፡- ማድረግ የሚገባህን አድርግ ግን እራስህ ጠብቅ
- ✓ ኢሳያስ፡- ለምን ግን ይሔ ሁሉ ነፃነት

- ✓ ፍቀርተ፡- ባታድርግ ትዕዛዝ ብቻ ልለውጥህ ስለማልችል
- ✓ ኢሳያስ፡- እንደውም ከአሁን በኋላ አልቅምም አልጠጣም አላጨስም
- ✓ ፍቅርተ፡- /እየሳቀች/ ከልብህ ነው
- ✓ ኢሳያስ፡- አዎን ከልቤ ነው አሁንም አልሔድም
- ✓ ፍቅርተ፡- አልሔድም!
- ✓ ኢሳያስ፡- አዎን አልሔድም
- ✓ ፍቅርተ፡- ለምን
- ✓ ኢሳያስ፡- መሔድ ስለሌለብኝ
- ✓ ፍቅርተ፡- ጠብቁኝ መጣው ብለሃቸዋል እኮ
- ✓ ኢሳያስ፡- ብላቸውም አልሔድም
- ✓ ፍቅርተ፡- መሔድ አለብህ
- ✓ ኢሳያስ፡- አልሔድም
- ✓ ፍቅርተ፡- ትሔዳለ
- ✓ ኢሳያስ፡- አልሔድም
- ✓ /ትሔዳለህ አልሔድም ትሔዳለህ አልሔድም እየተባባሉ በመጨቃጨቅ ላይ እያሉ መብራት ይጠፋል/

.....ትዕይንት ሁለት ይቀጥላል .....

_____ // _____

<<ዘፀአት ትዕይንት ሁለት>>

✓ ትዕይንቱ ሲጀምር ኢሳያስ፣ ፍቅርተ እና ዮሐንስ ቁጭ ብለው ይታያሉ

✓ ኢሳያስ፡- ክርስትና ማለት እንደዚህ ውብ የሆነ ሕይወት ነው እንዴ

✓ ዮሐንስ፡- ምን ለማለት ፈልገህ ነው

✓ ኢሳያስ፡- ማለት የፊለኩትማ ያኔ ክርስትናን የማስበው ቀለል አድርጌ ነበር ቤተ-ክርስትያን መሔድ መሳለም በቃ ከዚህ የዘለለ ነገር ያለው አይመስለኝ ነበር

✓ ፍቅርተ፡- አንድ ቀን እግዚአብሔር ወደዚህ የበረከት ሕይወት እንደሚያመጣ አምን ነበር

✓ ኢሳያስ፡- እኔ በራሴ ተስፋ ብቆርጥ እሱ ግን በጭራሽ ተስፋ አልቆረጠብኝም ነበር

✓ ፍቅርተ፡- ሰው በሰው ላይ ሰው በራሱ ላይ ተስፋ ሊቆርጥ ይችላል እግዚአብሔር ግን በማንም ላይ ተስፋ በይመለሳሉ ተሰፋ እስከ መጨረሻዋ ሕቅታ ድረስ በትዕግስት ይጠብቀናል

✓ ዮሐንስ፡- ዛሬ ደግሞ ንግግራችሁ ሁሉ ምንም አይጥምም ኢሴ አንቺም ልትፀድቂ ክርስትያን ሆንሽ ማለት ነው

✓ ኢሳያስ፡- አዎን

✓ ዮሐንስ፡- የፈጣ ሳቅ ይስቅበታል

✓ ኢሳያስ፡- አንተም ብትሆን ካሰብክበት ጊዜ አለህ

✓ ዮሐንስ፡- ማን እኔ ይሔን ከመሰለ ሕይወትማ ወዴትም ንቅንቅ አልልም

✓ ፍቅርተ፡- እሱ የምርጫህ ነው ጆኒ እንደ እህትነቴ ግን አንድ ነገር ብቻ ልንገርህ ተለወጥ ስላልኩ እንደማትለወጥ አውቃለው ያለህበት ሕይወት ግን ጥሩ እንዳልሆነ እራስህን አሳምን አንድ ቀን ትለወጥ ይሆናል

✓ ዮሐንስ፡- ሺህ ዘመን አልኖር

- ✓ ኢሳያስ፦ ይገርምሃል ፍቅር በመከረችኝ መሠረት ሁሉን ነገር ትቼ የቅድስት አርሴማን ጸበል ለመጠመቅ ወደ ገዳሟ ሔድኩ በዚያም መጠመቅ ጀመርኩ ተጠምቄ ከወጣው በኋላ ሲጋራ አጨስ ነበር በነጋታው ደግሞ ሔጀ እጠመቃለው በዚህ ሁኔታ ለተከታታይ ሦስት ቀናት ተጠመኩ በአራተኛው ቀን ግን ....
- ✓ ዮሐንስ፦ በአራተኛው ቀን ምን
- ✓ ኢሳያስ፦ እንደለመድኩት ተጠምቄ ከወጣው በኋላ ሲጋራዬን አጨስኩ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ግን በሕይወቴ ገጥሞኝ በማያውቅ ሁኔታ ክፉኛ ታመምኩ በሰዎች ሽክም እጠመቅበት ወደ ነበረው ፀበል ተወስድኩ ያጠምቁኝ የነበሩት አባት ጸበል ካጠመቁኝ በኋላ ትንሽ ተረጋጋው .... ምን እንዳደረኩ ጠየቁኝ እኔም አደርግ የነበረው ሁሉ ነገርኳቸው የአባትነት ምክራቸውን ሰጥተውኝ ዳግመኛ እንደዚህ እንዳላደርግ አስጠነቀቁኝ እኔ ከዚያች ቀን ጀምሮ ሁሉም ነገር አስጠላኝ ይሔው ዛሬ ያ ሁሉ አልፎ ከነበርኩበት የእርኩሰት ሕይወት ወጥቼ በጌታ አዲስ ሰው ለመሆን በቃው
- ✓ ፍቅርተ፦ እግዚአብሔር ማለት በድርጊት የሚገለፅ ፍቅር ነው
- ✓ ኢሳያስ፦ ብርቱ ቃል ቢኖረኝ ከዚህም በላይ አድርጌ ነበር የምገልፀው ግን ያው በውስጤ ያለውን የእሱን ማንነት እንዲህ ነው ብዬ ብዝርዝር ባይገልፅልኝም ከዚህ በላይ ነው።
- ✓ ፍቅርተ፦ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በስራ ላይ ነው ወይ እኛን እየሰራ አልያም ለእኛ እየሰራ ሰዎች ግን አናስተውልም እኛን እየሰራ ባለበት ወቅት ለእኛ እንዲሰራልን እንፈልጋለን እሱ ግን ለእኛ ከመስራቱ በፊት እኛን ሊሰራን ይፈልጋል
- ✓ ኢሳያስ፦ እሺ ዮሐንስ ምን ታስባለህ
- ✓ ዮሐንስ፦ ምንም
- ✓ ኢሳያስ፦ እንዴት ምንም ሳያስቡ የሚኖሩ እንስሳት ብቻ ናቸው
- ✓ ዮሐንስ፦ አንተም ዛሬ ተለወጥክና እንስሳ አልከኝ
- ✓ ኢሳያስ፦ እንደዚህ ማለቴ እኮ አይደለም .....
- ✓ ፍቅርተ፦ ማናችንም ከማናችንም አንበልጥም ሁሉም በድለዋል ሁሉም የእግዚአብሔር ክብር ጎሏቸዋል ነው የሚለው መፅሐፍ ቅዱስ ዋናው ቁምነገሩ ስህተትንና በደልን ማመንና አለማነን ላይ ነው
- ✓ ዮሐንስ፦ በእኔ ሕይወት ማንም ጣልቃ እንዲገባ አልፈልግም የሚጠቅመኝንና የሚጎዳኝን ነገር አውቃለው ስለምክራችሁ አመሰግናለው
- ✓ ኢሳያስ፦ ይሔውልህ ዮሐንስ ምንም ይሁን እኔና አንተ .....

- ✓ ዮሐንስ፡- ከአሁን በኋላ ሁለታችንም በወሰንበትን ጎዳና መጓዝ ይኖርብናል መልካም ህይወት /ወጥቶ ይሔዳል/
- ✓ ኢሳያስ፡- /ያዝናል/
- ✓ ፍቅርተ፡- ከሃገር መለየት ከቤተሰብ መራቅ ከጓደኛ መጣላት በክርስትና ሕይወት ይህም አለ ተለይተህ የምትወጣበት ጊዜ ይመጣል ስለሌላ ስለምን ስትል አይደለም ስለ ክርስቶስ ፍቅር ስትል ብቻ አይዞህ ኢሴ አትዘን በምንም ጉዳይ እኔ አጠገብህ ነኝ በዚህ ሰዓት ማዘን ሳይሆን መደሰት ነው የሚገባን
- ✓ ኢሳያስ፡- እንዴት ፍቅር
- ✓ ፍቅርተ፡- የሆነ ወቅት ላይ የአንተ የመሰሉህ ብዙ ወዳጆች ይኑሮሃል እውነተኛ ወዳጅ ጓደኛ እሰከመጨረሻው ድረስ ከንተ ጋር ይጓዛል ያልሆነው ግን በየመሃሉ እየተንጠባጠበ ከመንገድ ይቀራል እኔ ጋር ብዙ መፅሐፍቶች አሉ ታነባቸዋለህ ትተዋወቃቸዋለህም እውነተኛ ጓደኛ ለአፍህ ጣፋጭ ለመንገድህም ብርሃን ይሆኑሃል .. እሺ
- ✓ ኢሳያስ፡- እሺ በነገሮች ሁሉ ግን አንዳትለይኝ
- ✓ ፍቅርተ፡- አልለይህም ከአጠገብህ ነኝ .....ኢሴ
- ✓ ኢሳያስ፡- አቤት ፍቅር
- ✓ ፍቅርተ፡- በጣም እድሃለው
- ✓ ኢሳያስ፡- እኔም በጣም ወድሻለው

✓ ሁለቱም ይተቃቀፉሉ መብራት ይጠፉል

ተ...ፈ...መ

መወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን!

ድርሠት፡ ፋሲል ኪዳኔ